DeKalb County
School District

# የ DeKalb County የት/ቤትአውራጃ
# FY17 የወላጅ ተሳትፎ ፖሊሲ
## የግምገማ እና የክለሳ ቀናት
## ሜይ 25፣ ጁን 1፣ ጁን 7፣ ጁን 8፣ ጁን 9፣ ጁን 14፣ ጁን 21 እና ጁን 27/2016

**የ DeKalb ራዕይ የማህበረሰባችን ተማሪዎች በትምህርት መላቅን እንዲጎናጸፉ ለማነሳሳት ነው።**

**የ DeKalb ተልዕኮ ወደ ከፍተኛ ትምህርት፣ ስራ እና የእድሜ ልክ ትምህርት የሚያመራ የተማሪ ስኬታማነትን ማረጋገጥ ነው።**

**የ DeKalb መመሪያ መነሳሳት፣ ማግኘት እና መላቅ ነው።**

1. የ **DeKalb County ት/ቤት አውራጃ** በ ESEA ክፍል 1112 መሰረት በአውራጃ-ደረጃ ያለውን የወላጅ ተሳትፎ እቅድ ወላጆችን ባሳተፈ የጥምረት እድገት ላይ የሚከተሉትን እርምጃዎች ይወስዳል:-
   A. **አመታዊ ርዕስ I የወላጅ ተሳትፎ/ፖሊሲ ስብሰባ ያደርጋል።**
   B. **የርዕስ I ቅድመ-እቅድ ስብሰባ ያደርጋል።**
   C. **በድህረ-ገጽ እና በተለያዩ የመገናኛ ብዙሀን በወቅቱ ለወላጆች ያሳውቃል።**

2. የ **DeKalb County ት/ቤት አውራጃ** በ ESEA ክፍል 1116 መሰረት በሚደረገው ክለሳ እና ማሻሻያ ሂደት ላይ ወላጆችን ለማሳተፍ የሚከተሉትን እርምጃዎች ይወስዳል:-
   A. **አመታዊ አጠቃላይ የ LEA ማሻሻያ እቅድ (CLIP) ስብሰባ ያደርጋል።**
   B. **ቀጣይነት ያላቸው አስተያየቶችን ወላጆች እንዲጋሩ እድል ይሰጣል።**
   C. **በስብሰባ ወቅት ለወላጆች አስተርጓሚ ያቀርባል።**

3. የ **DeKalb County ት/ቤት አውራጃ** የተማሪ የትምህርት ስኬታማነትን እና የት/ቤት ብቃትን ለማሻሻል ውጤታማ የወላጅ ተሳትፎ እንቅስቃሴዎችን ለማቀድ እና ለመተግበር የሚከተለውን አስፈላጊ ማስተባበር፣ የቴክኒክ እገዛ እና የርዕስ I፣ ክፍል ሀ ት/ቤቶችን ለመርዳት ሌላ እገዛ ይሰጣል:-

**ሀ. ለወላጅ ተሳትፎ የማዕከላዊ ጽ/ቤት እገዛ - (ርዕስ I ዳይሬክተር፣ ረዳት ዳይሬክተሮች፣ የ OFP አስተባባሪዎች፣ የአውራጃ የወላጅ ተወካይ ጽ/ቤቶች እና አስተዳደራዊ እገዛ)።**
**ለ. የወላጅ ተሳትፎን የሚደግፉ 5 በአውራጃ-ደረጃ ያሉ የወላጅ ማዕከላት።**
**ሐ. በት/ቤቶ ድጋፍ የሚደረግለት የአካባቢ የወላጅ ማዕከላት - 36 በት/ቤት-ደረጃ የወላጅ ተወካይ ጽ/ቤቶች።**
**መ. ርዕስ I የቴክኒክ እገዛ እና የስራ ክፍለ ጊዜዎች።**
**ሠ. ርዕስ I የማክበር እና መመሪያ መርሆዎች ከፍተኛ ስብሰባ**
**ረ. የርዕስ I ማሻሻያዎችን ለማሳወቅ ወርሀዊ የርዕስ I መርሆዎች ስብሰባ ማድረግ።**

4. The **የ DeKalb County ት/ቤት አውራጃ**በክፍል ሀ የሚገኙትን የወላጆች ተሳትፎ ስልት ከሚከተሉት ሌሎች መርሀግብሮች ጋር ያስተባብራል እንዲሁም ያጣምራል:- [መርሀግብሮችን ያስገቡ፣ ለምሳሌ:- ሄድ ስታርት፣ ኢቨን

DeKalb County School District

ስታርት፣ ወላጆች እንደ መምህራን፣ ለቅድመ-ት/ቤት ህጻናት የቤት ውስጥ ትምህርት መርሀግብር እና በክልል-የሚሰራ የቅድመ-ት/ቤት መርሀግብር በሚከተለው የተዘጋጀ፡-

**A. የወላጅ ተሳትፎ ስልቶችን ለማገዛ የተመደበ ሰራተኛ።**

5. **<u>የ DeKalb County ት/ቤት አውራጃ</u>** ወላጆችን በማካተት የዚህን የወላጆች ተሳትፎ ፖሊሲ የርዕስ I፣ ክፍል ሀ ት/ቤቶችን ጥራት ከማሻሻል አንጻር የይዘቱን እና ውጤታማነቱን አመታዊ ግምገማ ለማድረግ የሚከተሉትን እርምጃዎች ይወስዳል። ግምገማው በወላጆች ተሳትፎ እንቅስቃሴዎች ላይ የወላጆችን የበለጠ ተሳትፎ የሚከለክሉ ነገሮችን መለየትን ያካትታል፤ (ዝቅተኛ ኢኮኖሚ ያላቸው፣ አካል ጉዳተኛ፣ በእንግሊዝኛ ቋንቋ የተወሰነ ብቃት ያላቸው፣ መጻፍ እና ማንበብ የማይችሉ ወይም ማንኛውም የዘር እና የብሄር በቁጥር አናሳ የሆኑ ወላጆችን የበለጠ ትኩረት ይሰጣል)። የት/ቤቱ አውራጃ ስለወላጆች ተሳትፎ ፖሊሲው እና እንቅስቃሴዎቹ በተደረገው ግምገማ የታዩ ግኝቶችን ለበለጠ ውጤታማ የወላጅ ተሳትፎ ስልቶችን ለመቅረጽ እና አስፈላጊ ከሆነ (እንዲሁም ወላጆችን በማካተት) የወላጅ ተሳትፎ ፖሊሲዎቹን ለማሻሻል ይጠቀምበታል።

**A. በዋና የስርዐተ-ትምህት ዳይሬክተር፣ መመሪያ እና በባለሙያ ትምህርት እንዲሁም በፌደራል መርሀግብሮች ጽ/ቤት በተዘጋጀው መሰረት የመርሀግብር ግምገማውን ይዶግሙ እንዲሁም ያጠናቁ፤ በመርሀግብሩ ግምገማ ለሚካተተው የወላጆች ተሳትፎ ጥራት አስፈላጊ የሆነውን የወላጅ ግብአትም ይሰብስቡ። አውራጃው በድህረ-ገጹ በሚገኘው የአውራጃው ሰፊ የዳሰሳ ጥናት በቀጣይነት ከወላጆች አስተያየት ይቀበላል።**
**B. በአውራጃ-ደረጃ ከተደረገ የዳሰሳ ጥናት የተገኘ የወላጆች አስተያየት።**

6. **<u>DeKalb County ት/ቤት አውራጃ</u>**ሰፊ ለበለጠ ጠንካራ የወላጅ ተሳትፎ፣ ውጤታማ የወላጅ ተሳትፎን ለማረጋገጥ እና የተማሪ የትምህርት ውጤታማነትን ለማሻሻል በሚመለከታቸው ት/ቤቶች፣ ወላጆች እና ማህበረሰብ መካከል ሽርክናን ለመደገፍ ተለይተው ከስር በተገለጹት እንቅስቃሴዎች የት/ቤቱን እና ወላጆችን አቅም ይገነባል፡-

ሀ. የት/ቤቱ አውራጃ በርዕስ I፣ ክፍል ሀ ት/ቤቶቹ እገዛ ጋር በት/ቤት አውራጃው ወይም በት/ቤቱ ለሚገለገሉ ልጆች ወላጆች እንደአስፈላጊነቱ በዚህ አንቀጽ የተገለጹትን እርምጃዎች በማካሄድ እገዛ ያደርጋል፤ ለዚህም የሚከተሉትን ርዕሶች በመረዳት መሆን አለበት፡-

- የክልሉን የትምህርት ይዘት ደረጃዎች፣
- የክልሉን የተማሪ ትምህርት ስኬታማነት ደረጃዎች፣
- የክልሉን እና የአካባቢውን የትምህርት ግምገማዎች፣ አማራጭ ግምገማዎችን ጨምሮ፣
- የክፍል ሀ መስፈርቶች፣
- የልጃቸውን ለውጦች እንዴት እንደሚቆጣጠሩ እና
- ከአስተማሪዎች፣ ወላጆች እና የሚመለከታቸው አካላት ጋር እንዴት እንደሚሰራ፡-

**ይህን የሚያግዙ ሁኔታዎች የሚከተሉት ናቸው፡-**

1. **ርዕስ I የወላጅ ተሳትፎ ስብሰባ (የአውራጃ እና የክልል)።**
2. **አጠቃላይ የ LEA ማሻሻያ እቅድ (CLIP)(አመታዊ)።**
3. **ርዕስ I የወላጅ ተሳትፎ ፖሊሲ ስብሰባ (አመታዊ)።**
4. **ተለዋዋጭ የመማሪያ መርሀግብር ስብሰባዎች (FLP)።**

DeKalb County School District

5. **የወላጅ ወርክሾፖች (ለምሳሌ Georgia Milestone፣ Infinite Campus ወዘተ)**
6. **በአውራጃ-ደረጃ የሚደረግ ርዕስ I የወላጅ ስብሰባ።**

ለ. የት/ቤት አውራጃው ከት/ቤቶቹ እገዛ ጋር ወላጆች ከልጆቻቸው ጋር እንዲሰሩ ለማገዝ፣ ማለትም የልጆቻቸውን የትምህርት ስኬታማነት ለማሻሻል ቁሳቁሶች እና ስልጠናዎችን ይሰጣል፣ ለምሳሌ በሚከተለው የወላጅ ተሳትፎን ለማበረታታት የመጻፍ እና የማንበብ ስልጠና እና እንደአስፈላጊነቱ የቴክኖሎጂ አጠቃቀም፡-

1. **የትምህርት ምንጮች እና መሳሪያዎች ላይ ለወላጅ ስልጠና መስጠት።**

ሐ. የት/ቤት አውራጃው ከት/ቤቶቹ እና ወላጆች እገዛ ጋር በመሆን መምህራኖቹን፣የተማሪ አገልግሎቶች ሰራተኛ፣ ርዕሰ-መምህራኖቹን እና ሌሎች ሰራተኞችን እንደ ወላጅ ሆነው፣ በወላጅ የዋጋ እና የጥቅም አስተዋጽኦ እንዴት ወላጆችን ማግኘት፣ ከወላጆች ጋር መነጋገር እና መስራት እንዳለባቸው እንዲሁም የወላጅ መርሀግብሮችን እንዴት ተግባራዊ እንደሚያደርጉ እና እንደሚያስተባብሩ እንዲሁም በወላጆች እና በት/ቤቶች መካከል ትስስር እንዴት እንደሚፈጥሩ በሚከተለው መንገድ ያስተምራል፡-

1. **ለት/ቤት አስተዳደሮች/ርዕሰ-መምህራን እና/ወይም የተመደበ ሰራተኛ ወርሀዊ ስብሰባዎች።**
2. **በርዕስ I ለሚደጎም ሰራተኛ የባለሙያ ሰራተኛ።**
3. **ርዕስ l የማክበር እና መመሪያ መርሆዎች ከፍተኛ ስብሰባ**

መ. የት/ቤት አውራጃ በተቻለ መጠን እና እንደአስፈላጊነቱ የወላጅ ተሳትፎ መርሀግበሮችን ከሄድ ስታርት፣ ኢቨን ስታርት፣ ለቅድመ-ት/ቤት ህጻናት የቤት ውስጥ ትምህርት መርሀግብር፣ ወላጆች እንደ መምህራን መርሀግብር እና የህዝብ ቅድመ-ት/ቤት እና ሌሎች መርሀግብሮች ጋር ያስተባብራል እንዲሁም ያጣምራል፤ እንዲሁም ሌሎች እንቅስቃሴዎችን ለምሳሌ ወላጆች በልጆቻው ትምህርት በበለጠ እንዲሳተፉ የሚያበረታታ እና የሚያግዝ የወላጅ የምንጭ ማዕከላትን በሚከተለው ሁኔታ ያደርጋል፡-

1. **ከፌደራል መርሀግብሮች ጽ/ቤት (OFP) እገዛ ይሰጣል።**
2. **በአምስቱ ክልላዊ ማዕከላት እና ሰላሳ ስድስት የት/ቤት ማዕከላት ለሚገኙት ማዕከላት ወላጆች ተደራሽነት እንዲኖራቸው ያደርጋል።**
3. **የማህበረሰቡን፣ ወላጆችን እና የሚመለከታቸውን አካላት ፍላጎት ለማሟላት ለክልል ማዕከላት በሳምንት አንድ ቀን ሰአታትን መጨመር።**

ሠ. ከት/ቤቱ እና ከወላጅ መርሀግብሮች፣ ስብሰባዎች እና ሌሎች እንቅስቃሴዎች ጋር በተያያዘ ለተሳታፊ ልጆች ወላጆች ሊገባ በሚችል እና በተመሳሳይ ፎርማት ማለትም በጥያቄ የሚደረጉ አማራጭ ፎርማቶችን ጨምሮ እንዲሁም ተግባራዊ መሆን እስከሚችለው ድረስ፣ ወላጆቹ በሚረዱት ቋንቋ መረጃ መድረሱን ለማረጋገጥ የት/ቤት አውራጃው የሚከተሉትን እርምጃዎች ይወስዳል፡-

DeKalb County School District

1. **የወላጅ ተሳትፎ ንግግሮችን በተለያዩ ቋንቋዎች እና ፎርማቶች ማሳወቅ (ለምሳሌ በማህበረሰብ ጋዜጣዎች፣ በራሪ ወረቀቶች፣ ድህረ-ገጾች፣ ማህበራዊ ድህረ-ገጾች ወዘተ)**
2. **ከወላጆች ጋር ለመገናኘት የተለያዩ የመገናኛ ብዙሀን መንገዶችን መጠቀም።**
3. **ንግግሮችን ወደ ተቀዳሚ አስር ቋንቋዎች ማስተርጎም።**
4. **የአውራጃው ፖሊሲ በአመታዊ ርዕስ I የወላጅ ስብሰባ ላይ ይገለጻል።**

ረ. ወላጆች ሊጠይቁ ስለሚችሉ በክፍል 1118 መሰረት ለወላጆች ተሳትፎ እንቅስቃሴዎች ሌሎች ምክንያታዊ እገዛዎችን መስጠት ።

1. **ወላጆች ሀሳባቸውን ሊያጋሩ ስለሚችሉ እና ሀሳቦቹንም ለመርዳት ድጎማዎች ሊኖሩ ስለሚችሉ የወላጅ ተሳትፎ ዝግጅቶችን ማቀድ።**

## <u>በስራ ላይ መዋል</u>

ይህ በአውራጃ-ደረጃ የሚገኝ የወላጅ ተሳትፎ ፖሊሲ በጥምረት የተዘጋጀው እና ስምምነት ተደረገው በርዕስ I፣ ክፍለ ሀ መርሀግብሮች ላይ ከሚሳተፉ ልጆች ወላጆች ጋር በወላጆች ተሳትፎ ፖሊሲ ግምገማ እና ክለሳ ስብሰባ ላይ በሚከተለው ጊዜ ነው፡- (ቀናት) ሜይ 25፣ ጁን 1፣ ጁን 7፣ ጁን 8፣ ጁን 9 & ጁን 14፣ ጁን 21 እና ጁን 27/2016፣ (ጊዜ) 9:00 am - 11:00 am;  11:00 am  – 1:00 pm; 1:00 pm - 3:00 pm; 5:00 pm - 7:00 pm; & 4:00 pm - 5:00 pm. ስብሰባዎቹ በሚከተሉት ቦታዎች ተካሂደው ነበር፡- የ DeKalb County የስብሰባ ክፍል፣ McClendon ES፣ Stoneview ES እና Stephenson MS።

**ይህ ፖሊሲ በስራ ላይ የዋለው በ<u>DeKalb County ት/ቤት አውራጃ</u> ሲሆን <u>ከኦገስት 2016 - ኦገስት 2017</u> ድረስ በስራ ላይ ይውላል።_የት/ቤቱ  አውራጃ ይህን ፖሊሲ በርዕስ I፣ ክፍለ ሀ ላይ ለሚሳተፉ ልጆች ወላጆች ሁሉ በሴፕቴምበር 15/2016 ወይም ከዛ በፊት ያሰራጫል።**

DeKalb County
School District

## የዳሰሳ ጥናት ግምገማ

## ዋጋ እንሰጥዎታለን፣ ግብአትዎ ለኛ ዋጋ አለው

1. ርዕስ I የአውራጃ የወላጅ ተሳትፎ ፖሊሲን በተመለከተ ተጨማሪ አስተያየት ወይም ምክር አለዎት?

| |
|---|
| |
| |
| |
| |
| |

2. 1% የወላጅ ተሳትፎ ርዕስ I ድጎማዎች እንዴት በስራ ላይ እንደዋሉ ማወቅ ይፈልጋሉ?

| |
|---|
| |
| |
| |
| |
| |

3. የአውራጃውን ፖሊሲ የወላጅ ተሳትፎ ግምገማ እና ክለሳ በተመለከተ ተጨማሪ አስተያየት ሀሳብ ወይም ምክር አለዎት?

| |
|---|
| |
| |
| |
| |
| |

**የ DeKalb County ት/ቤት አውራጃ የወላጅ ተሳትፎ ፖሊሲ ሴፐቴምበር 15/2016 ተሻሽሎ በስራ ላይ ዋለ፣ ይህ ፖሊሲ የአውራጃውን ራዕይ፣ ተልዕኮ እና መመሪያ ያሳያል።**